ባሕሩ ዘውዴ፣ *ኅብር ሕይወቴ፤ ግለ ታሪክ*፤ አዲስ አበባ፣ ኢክሊፕስ ማተሚያ ቤት፣ 2015 ዓ.ም.፤ የገጽ ብዛት 313።

ባለፉት ዓመታት በአገራችን ቁጥራቸው ቀላል በማይባል ሰዎች የተሰነዱ የሕይወትንና የሥራ ልምድን መሠረት ያደረጉ ግለ ታሪኮች ለአንባብያን እየቀረቡ ይገኛሉ። አብዛኛዎቹ ሥራዎች በውትድርና ሙያ በነበሩ፣[1] በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ባገለገሉ፣[2] በተለያዩ የግልም ሆነ የቅጥር ሥራ የከበረ የሕይወት ልምድ ባካበቱና[3] በኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል ታሪክ ውስጥ ተሳትፎ በነበራቸዉ ግለሰቦች[4] የተፃፉ ሲሆኑ በጣም የተወሰኑት ደግሞ ከአካዳሚው ዓለም በመጡ ምሁራን[5] የቀረቡ ናቸው። አንዳንዶቹ ግለ ታሪኮች የጸሐፊዎቹን ሕይወትና ልምድ ከመጀመሪያው አንስቶ (ቤተሰብን፤ ውልደትን፤ ልጅነትን፤ ዕድገትንና የሕይወት ተሞክሮን ጨምሮ) የሚተርኩ ሲሆኑ፤ ሌሎቹ በጸሐፊው የተወሰኑ የሥራና የሕይወት ድርጊቶች ወይንም ተሞክሮዎች ላይ የሚያጠነጥኑ ናቸው ።[6] እነዚህ ሥራዎች የጸሐፊዎቹን ሕይወትና ልምድ ከማሳየት ባለፈ እነሱ የኖሩባትና ያገለገሏት፤ ብዙም ስኬት ያዩባት ብዙም ችግሮች ያሳለፉባት ኢትዮጵያን ከፍ ሲልም ዓለምን አንባብያን እንዲያዩ፣ ከተቻለም እንዲመረምሩ ያስችላሉ። እንደዚህ ዓይነት የታሪክ ተማሪዎች ለታሪክ ጥናት ግብዓት የሚሆኑ ተዝቀው የማያልቁ መረጃዎች የሚያገኙባቸው ናቸው።

በታሪክ የትምህርትና የምርምር ሙያ በተሰማራ ምሁር የተፃፈ ግለ ታሪክን በተመለከተ ግን የፕሮፌሰር ባሕሩ ዘዉዴ "ኅብር ሕይወቴ፤ግለ ታሪክ" ሁለተኛው ነው ።[7] በዚህም ጸሐፊው ባንድ በኩል በሌላው ዓለም የተለመደውን፣ በኢትዮጵያ ደግሞ በቅርቡ የተጀመረውን ግለ ታሪክን የመጻፍ ባህል የተቀላቀሉ ሲሆን በሌላ በኩል የታሪክ ጥናትን በተመለከተ ፈር ቀዳጅ የሆነ በኢትዮጵያዊ የታሪክ ተመራማሪ በአማርኛ ቋንቋ የተሰነደ ግለ ታሪክ ለአንባብያን አቅርበዋል።

ብዙዎች፣ በተለይም በታሪክ ምርምርና ማስተማር ሥራ ላይ የተሰማሩ ባልደረቦቻቸው የሚመኙት ተስፋም ዕምነትም የሚያደርጉት ይህ የተጀመረው ሥራ እንዲቀጥል፤ ሌሎችም እንዲጽፉና እንዲያሳትሙ፣ በዚያውም የነሱንም ሆነ የዘመናቸውንም ታሪክ፤ ታሪኩንም ያዩበትን ዕይታና ምርመራ ለአንባብያንም ለተከታዩ ትውልድም እንዲያቀርቡ ነው።

## *እንደ መግቢያ*

"ኀብር ሕይወቴ ግለ ታሪክ" 313 ገፅ ያለው በ2015 ዓ.ም. የታተመ በታሪክ ሙያ በሠለጠነ ተመራማሪ የተጻፈ ሁለተኛ ሥራ ነው:: ከርዕሱ ብንጀምር፣ የመጽሐፉ ቁልፍ ሐሳብ "ኀብር" የሚለው ቃል ሲሆን፤ በመጽሐፉ የፊት ገፅ ላይ በሚታየው የተጠላለፈ ገመድ ተመስሎ ቀርቧል:: ይህን ሐሳብ በተለያየ መንገድ ማየት ይቻላል:: ባንድ በኩል የተጋመደውን፤ ተነጣጥሎ ለማየት የሚከብደውን አካዳሚያዊ፤ ማኀበራዊና ፖለቲካዊ ሕይወታቸውን ያመለክታል:: በሌላ በኩል ንብርብርነትን፣ በዚህም በተለያየ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ምክንያቶች የተሠሩና የዳበሩ ድንበር ዘለል የሆኑ ሰዋዊ፤ አካባቢያዊ (ገጃነትን፣ ጉራጌነትን፣ አዲስ አበቤነትን)፣ አገራዊ (ኢትዮጵያዊነትን)፤ አህጉራዊና (አፍሪካዊነትን) ዓለም አቀፋዊ ማንነታቸውን ያሳያል::

ከ "ኀብር" ወይንም " "ኀብራዊነት" በተጨማሪ የመጽሐፉ የፊት ገፅ ሌላ የጸሐፊውን መለያ የሕይወት መርሆንም ይዟል:: ወዳጆቻቸው እንደሚያውቁት ወይንም እንደነገሯቸው፣ ጸሐፊው ሕይወታቸውን በሦስት አዕማድ ላይ መሥርተው፣ የሦስቱንም ሚዛን አስጠብቀው፣ አካዳሚውን ከሌሎቹ ቢያስበልጡም አንዱንም ግን ሳያጓድሉ አርቀው፣ አስማምተዉ መምራት መቻላቸው ነው::

አሁን ደግሞ ከመጽሐፉ የፊት ገፅ ወጥተን ወደ ውስጥ ገፆቹ እንዝለቅ:: መቅድምን ሳይጨምር መጽሐፉ በአስራ አምስት ክፍሎች በመከፋፈል የትውልድ ሀረጋቸውን፣ ልጅነታቸውን፣ በሀገር ውስጥም፣ ከሀገር ውጭም የነበራቸውን ከመሰናዶ ጀምሮ እስከ የታሪክ ሦስተኛ ዲግሪ ድረስ የዘለቀ ትምህርታቸውን፤ እንዲሁም ደግሞ በአካዳሚው ዓለም የማስተማር የምርምርና ተቋማትን የመምራት አስተዋፆአቸውን ይተርካል:: በተጨማሪም የትዳር ሕይወታቸው፣ በውጭ ሀገራት ያደረጓቸው ሙያዊ ጉብኝቶችና ቆይታዎች፣ የደርግ ዘመን የእስር ቆይታቸው፣ በመንግሥት ጥያቄ የተበረከቱ አገልግሎቶች (ጸሐፊው "የዕብደት ዘመቻ" የሚሉትን በመተከልና ጋምቤላ የተደረገውን የሰፈራ ሂደትን ጨምሮ)፤ በመጨረሻም በሀገራዊና አህጉራዊ የሲቪል ማኀበረሰብ ውስጥ የነበራቸው ተሳትፎ በስፋትና ቀልብን በሚስብ ቋንቋ ይተነትናሉ::

“ኀብር ሕይወቴ”፤ እንደ ታሪክና (History) ትርክት (Historiography)

የፕሮፌሰር ባሕሩ መጽሐፍ በያዘው መረጃ ብቻ ሳይሆን መረጃዎቹ በተመረጡበት፤ በተተነተኑበትና በተጻፉበት መንገድ ሲመረመር ስለግለ ታሪክ ምንነት፤ የታሪክ ጥናትና አጻጻፍ ታሪክ ላይ የሚነሱ ሐሳቦችን የሚያጠናክር ሆኖ እናገኘዋለን።

ለምሳሌ ከአጻጻፉ ብንነሳ ከአካዳሚክ ጽሑፎች በተለየ ግን ባልራቀ መንገድ “ኀብር’ ሥነ ጽሑፋዊ ዘዬዎችን ይጠቀማል። ትርክቱም ለአንባብያን እንዲመች ወይንም እንዲስብ አባባሎችን፣ ምሳሌዎችንና ቃላቶችን በተለያየ ቦታና መንገድ ሥራ ላይ ሲውሉ እናያለን። የጸሐፊውን አካዳሚክ ሥራዎች በተመለከተ በተደጋጋሚ የሚጠቀሱ መለያዎች ምርምሮቹ ጥልቅ፤ ጥንቁቅና፤ ሚዛናዊ ብቻ ሳይሆኑ የተጻፉባቸው መንገዶችና ቋንቋ ቀለል ያሉ፤ ግልፅ የሆኑ፤ አጭርና ያልተንዛዙ መሆናቸው ነው። በኬምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ተመራማሪ የነበረውን ጆርጅ ትሬቬሊያንን (George Trevelyan, 1876-1962) ምክርና አጻጻፍ በመጥቀስ ተማሪዎቻቸው ጥናቶቻቸውን በሚገባ፣ በሚቀልና በሚስብ መንገድ እንዲሰንዱና እንዲያቀርቡ ያበረታቱ እንደነበር ተማሪዎቻቸው የነበሩ ያስታውሳሉ።

ከታሪክ አፃፃፍ ጥናት አኳያ ከታየ የግለ ታሪክ ሥራ ጸሐፊውንና ጽሑፋቸውን እንደ አንድ ተዓማኒነት እንዳለው የመረጃ ምንጭነት እንዲቆጠሩ የሚያደርጋቸዉንም ዕድል ፈጥሮላቸዋል። በዚህ አጋጣሚ መጠቀስ ያለበት አንድ ቁም ነገር ቢኖር በአካዳሚክ ታሪክና በታሪክ አጥኝ በሚፃፍ ግለ ታሪክ መሃከል የቀረበ ተጨባጭና ሃልዎታዊ (methodological) ግንኙነት መኖሩን (ለምሳሌም ሁለቱም የትርክትን አጻጻፍ መከተላቸው)፣ ‘ሳይንሳዊ’ በሚባለውና ‘ሥነ ጽሑፋዊ’ በሆነው ጸሐፊ ወይንም ሥራ ያለው አጥር ሁሌም የጠበቀ ሳይሆን አንዳንዴም የላላ እንደሆነ፤ ለምሳሌም ግለ ታሪክ ሁሌም አእምሮዓዊ ማለት አለመሆኑን፤ ገለልተኝነት ወይንም ገለልተኛ ዕውቀት የሚሠራው ለአካዳሚክ ብቻ ሳይሆን ለግለ ታሪክም እንደሆነ ነው። ይህ ማለት ግለ ታሪክ የሚጽፉ የታሪክ አጥኚዎች ለግለ ታሪክ አጻጻፍ ከተፈቀዱ ወይንም ከሚዘወተሩ አሠራሮች በተጨማሪ በአካዳሚክ ምርምር ዓለም የተለመዱ ሕግጋትንም ይከተላሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንዶቹን ሕግጋት፣ ለምሳሌ በታሪክ ጥናት ቁልፍ የሆነውን ገለልተኝነት የሚባለውን ህሳቤ፣ ሞጋችም ሆነው ሲሠሩ ይታያሉ።

በሌላ በኩል “ኅብር ሕይወቴ” ለጸሐፊዉ በአካዳሚክ ጽሑፎች ሊካተቱ በማይችሉ ወይንም በሚከብዱ ጉዳዮች ላይ፣ ለምሳሌም ስለውልደታቸውና ዕድገታቸው፣ ስለወላጆቻቸው፣ ቤተሰቦቻቸውና ጓደኞቻቸው፤ ስላደጉበት አካባቢና ስላሳደጋቸው ባህላዊ፣ ማኅበራዊና ዕውቀታዊ መቼት (setting) በነፃነትና ለቀቅ ባለ ቋንቋ ለመጻፍ አስችሏቸዋል። ግለ ታሪክ በተለምዶ አካዳሚክ የታሪክ ምርምር ከሚያተኩርባቸው መዋቅራዊ ከሆኑ ጉዳዮች ይልቅ የሰውን ውክልና በማጉላት፤ ከኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ወጣ በማለት ባህላዊና ማኅበራዊ በሆኑ አርዕስቶች ላይ በመመሥረት የተለመደው የታሪክ ምርምር የማያሳያቸውን ነገር ግን ቁልፍ የሆኑ የሰው ልጅ ታሪኮችን ለማጥናት አስችሏቸዋል ቢባል የተጋነነ አይሆንም።

በተለይም በአካዳሚክ ሕግጋት ውስጥ በማይበረታታው ነገር ግን የውስጥ ስሜትን ሊገልፅ በሚያስችል ቋንቋ (emotive language) እንዲጽፉ ዕድል ፈጥሮላቸዋል። እነኝህ ከላይ የተዘረዘሩት ጉዳዮች ቁልፍ የሕይወታቸው ታሪክ አካል ብቻ ሳይሆኑ የሙያዊ ዕድገታቸውን፤ ስለታሪክ፣ ስለታሪክ አጻጻፍ፣ ከዛም አልፎ ስለሀገር፣ ስለማንነት፣ ስለዓለም፣ ስለፖለቲካ ወዘተ ያላቸውን ዕይታና ፍልስፍና በመቅረፅ ቦታ የነበራቸው መሆናቸውን መገመት ይቻላል።

በዚህ በኩል በጸሐፊው የውልደት እንዲሁም የቤተሰብ ታሪክና በጸሐፊው የሕይወትና የሙያ ፍልስፍና መሃከል ግኑኝነት የለም ማለት አይቻልም። እንደዚሁም ባንድ በኩል የግል የሕይወት ልምዳቸውና ዕይታቸው፣ በሌላ በኩል በጋራ እንደ ማኅበረሰብ በነበረው ታሪክ መሃከል ያለውን ግንኙነት ላለማየት አይቻልም። ጥናቶችም እንደሚያሳዩት በግል ታሪኮችና በሙያ ወይንም በጥናት ምርጫዎች መሃከል ተደጋጋሚ መቀራረቦች እንደሚኖሩ ነው። ለምሳሌ ሮበርት ሮዘንስቶን የተባለው የታሪክ ተመራማሪ የታሪክ የጥናት ሥራዎቹ ምን ያህል የግል ታሪክ እንደሆኑ ያወቀው የራሱን ሕይወት፣ በተለይም የቤተሰቡን ታሪክ፣ መመርመር ከጀመረ በኋላ ነው ።

> ለሁለት ዐሠርት ዓመታት ምርምሮቼ ያተኮሩት ጥግ ባሉ ጉዳዮች (marginal characters) ማለትም በሁለት ባህሎች ተከፍለው ባሉ ሰዎች ላይ ነበር ። … ነገር ግን ይህ የጥናት ምርጫዬ ከራሴ ታሪክ ጋር ሊገናኝ ይችላል ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር። የተወለድክበት ተሰዳጅ ቤተሰብ እንደ ላትቪያና ሮሜኒያ ካሉ ሁለት የተለያዩና የሚቃረኑ ባህሎች የመጣ… ከሆነ በተለያዩ ዓለማት ባሉ እምነቶችና ባህሎች ተከፍለው (torn) ያሉ ገፀ ባሕርያትን [ማለትም ጉዳዮችና ሰዎችን] ለማጥናት ፍላጎት ብታሳይ አይደንቅም።[8]

በተጨማሪ በዚህ ትንታኔ ከተስማማን ተመራማሪው በግል ታሪካቸው አማካይነት የጋራ (ማለትም የሀገር) ታሪክን ጽፈዋል ማለት ይቻላል። ወይንም በራሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸዉና ጓደኞቻቸዉ ታሪክ በኩል አድማሱ የሰፋውን የሀገርን፣ በዛውም የዓለምን፣ ታሪክ ለማየትና ለማሳየት ሞክረዋል ብሎ መናገር ይቻላል። ይህ ማለት ጸሐፊው ራሳቸው ከራሳቸው ሕይወት በመነሳት እንደ ኢትዮጵያ አብዮትና የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ በመሳሰሉ ታላላቅ የሀገሪቱ የጋራ ታሪኮች ላይ በራሳቸው መነፅር፣ የነበራቸውንም የትግል ተሳትፎ ተጠቅመው፣ የራሳቸውን ምልከታ ማኖር የሚችሉበት አጋጣሚ አገኙ ማለት ነው። ተመራማሪው ያለፉበትን የሕይወት ታሪካቸውን በመተረክ ከአካዳሚክ ታሪክ በተለየ፣ አንዳንዴም በተሻለ፣ መንገድ ግለ ታሪክ ስላለፈው ዘመን ጠለቅ ያለ መረዳት እንዲኖር የሚያስችል ዘርፍ መሆኑን ማሳየት ችለዋል ማለት ይቻላል።

ይህንንም በምሳሌዎች ማሳየት ይቻላል። ባንድ በኩል የፕሮፌሰር ባሕሩ ግለ ታሪክ አርዕስት አመራረጥ፣ በመጽሐፉ ውስጥ ለቤተሰባቸው ታሪክ የተሰጠው ቦታ፣ በአጠቃላይ ከውልደታቸው እስከ ቅርብ ጊዜ የነበረውን ሕይወታቸውን የተረኩበት ሁኔታ ግላዊና የጋራ ማንነቶች እንዴት እንደሚሠሩና እንደሚለወጡ፤ እነኝህ ባህላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ሙያዊና ምሁራዊ ማንነቶች እንዴት እንደሚወከሉ፣ በተደጋጋሚ እንደሚገነቡና እንደሚለወጡ የሚያሳይ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ለምሳሌ የትውልድ ሀረጋቸውንና ልጅነታቸውን ቦታ ሰጥተው በመተረክ የራሳቸውንም ሆነ የአብዛኛው የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ የተገነባበትን ንብርብር የሆነ ታሪክና ባህል፤ ከጎጥ፣ ከቋንቋ፣ ከእምነትና ከቀዬነት የሰፉ ማንነትን መተንተን ችለዋል። የቤተሰባቸውን ታሪክ በመዘገብም ብዙ ኢትዮጵያውያንን የሚያመሳስለውን የድህነት ሕይወትንና ከድህነት ጋር የሚደረገው ትግል ምን እንደሚመስል አሳይተዋል። በቤተሰባቸው ስላሉት ሴቶች በተለይም ስለእናታቸው ያካፈሉት ትውስታ በኢትዮጵያ ታሪክ ሥራቸው ብዙ ስለሆነው፣ በማኅበረሰቡ ግን ተገቢውን ቦታ ስላልተሰጣቸው ሴት ኢትዮጵያውያን እንደገና እንድናስብ፣ እንድናጠና፣ የተሻለ መረዳትና ዕውቀት እንዲኖረን የሚገፋፋን መረጃ ነው። እነኝህን የመሳሰሉ ታሪኮች ለኢትዮጵያ፣ በተለይ ደግሞ በከተሞች ላለው ማኅበራዊ ታሪክ እንደ ምሳሌም የድህነት ታሪክ እና የሥነ ፆታ ታሪክ ምርምር ትልቅ ግብዓት የሚሆኑ ናቸው። እነኝህ የመጽሐፉ የመጀመሪያ ሁለት ክፍሎች ብዙም ያልተኬደበትን ነገር ግን ቁልፍ የሆነውን የማኅበራዊ ታሪክ አስፈላጊነትን እንዲያውም አስቸኳይነትን የሚያሳዩ ናቸው ቢባል ስህተት አይሆንም። በዚህም መጽሐፉ የሕይወት መረጃ ከማካፈል በተጨማሪ የጥናት አቅጣጫን ለመጠቆምም የሚረዳ ሥራ አበርክቷል ማለት ይቻላል።

የጸሐፊው የቅድመ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ጉዟቸው በዘመኑ የነበሩ ኢትዮጵያውያን የሚያልፉበትን ውጣ ውረድ ብቻ ሳይሆን የነበራቸዉንም የዕውቀት ጉጉት፤ ለስኬት የሚደረግ ግብግብንም ፍንትው አድርጎ ያሳየ ነው። በተለይ የጊዜው መምህራን፣ የውጭዎቹንም ጨምሮ፣ በተማሪዎች ዕድገት ላይ የነበራቸው አስተዋፅዖ ምን ያህል ከፍተኛ እንደነበረ በመተረክ የዘመናዊ ትምህርት በኢትዮጵያ የያዘውን ቦታ፤ የውጭው ዓለም በማስተማርም ሆነ በትምህርት ሥርዓት ቀረፃ የነበረውን ተፅዕኖ ለማሳየት የሚረዳ መረጃን አካፍለዋል። የመጀመሪያ ዲግሪ የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸው ከትምህርት ጉዳዮች በተጨማሪ በጊዜው በሀገሪቱ የነበረውን የለውጥ እንቅስቃሴ በአካዳሚክ የምርምር ስርዓት ከሚቀርቡት ትርክቶች በተለየ መንገድ በራሳቸው ተሞክሮ ዕይታና ቋንቋ በመዘገብ ለአንባብያን አቅርበዋል። ይህ ከትምህርታቸው ጋር የተጋመደው የሀገሪቷ የአብዮትና የለውጥ ታሪክ ወደውጭ ለከፍተኛ ትምህርት ሲሄዱም ሆነ ተመልሰው እስር ቤትም ሲገቡ አልተላቀቃቸውም። ይህ በጊዜው የነበሩ ተማሪዎችና ወጣቶች ታሪክ በተለያዩ ተመራማሪዎች ቢጠናም፤ ብዙ ጊዜ በግለ ታሪክ ሆነ በትውስታ መልክ ስለማይቀርብ ውስብስብ የሆነው የአብዮቱና የለውጡ ሂደት ፖለቲካዊ እንጅ ማኅበራዊ ታሪኩን በጥልቀት እንዳናውቅ ሆነናል። በዘመኑ ባለፉ እንደ ታሪክ አጥኝውም ዓይነት ባሉ የሚጻፉ ግለ ታሪኮች ስለዘመኑ፣ በጊዜውም ስለነበሩ የለውጥ ሐሳቦች፣ ትግሎችና የሕዝብ እንቅስቃሴዎች የተለየና የበለፀገ መረዳትን ይሰጡናል።

ስለእስር፣ በተለይም በፖለቲካ ምክንያት የሚመጣ አፈና፣ ስቃይና ግድያን በተመለከተ ግለ ታሪኮች ከአካዳሚክ ሥራዎች ባላነሰ ወይንም በተለየና በበለጠ መንገድ መረጃንና መረዳትን ይሰጣሉ። ብዙውን ጊዜ ስዕላዊና ከጥልቅ ስሜት ጋር ተቆራኝተው የሚጻፉ ናቸውና የተሻለ ተነባቢነትም ይኖራቸዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ አፈናና ስቃይ ታሪክ ለመጻፍ እንደ “ኅብር ሕይወቴ” ዓይነት ግለ ታሪኮች ቁልፍ ግብዓት ሆነው ያገለግላሉ። በሌላ በኩል ጸሐፊው በውጭ ሀገር በትምህርትና በምርምር ያሳለፏቸው ረጅም ዓመታትና ያካበቷቸው ልምዶች ከኢትዮጵያውያን የውጭ ልምድ ታሪክ፣ ከዛም ከፍ ሲል ከዲኣስፖራ ታሪክ ጋር የተቆራኘ ነውና ወደፊት በሚጻፉ ሰፊ፣ ጥልቅና የረጅም ጊዜ ታሪክ ስላለው የኢትዮጵያውያን (ከዛም አልፎ የአፍሪካውያን) የውጭ ኑሮና ተሞክሮ ታሪክ እንደ አንድ በጣም ጠቃሚ መረጃ ሆኖ ሊጠቀስ ይችላልና ለጉዳዩ ትኩረት ለሚሰጡ አንባቢዎችም ሆኑ ተመራማሪዎች መልካም አጋጣሚ ተፈጥሮላቸዋል ማለት ይቻላል።

በዩኒቨርሲቲ ያሉ ምሁራን ከሙያቸዉም ሆነ ከዋናው መሥሪያ ተቋማቸው ወጣ ብለው ሊሠሩ፣ ድርብርብ ሕይወቶችን ሊኖሩ እና ንብርብር ማንነቶችን ሊይዙ ቢችሉም፤ ዋናው ሙያዊና ምሁራዊ ማንነታቸው የተገነባው በአካዳሚክ ሥራቸውና ሕይወታቸው ነውና የዚህ ግለ ታሪክ ጸሐፊም በዋናነት መታየት ወይንም መገምገም ያለባቸው ከዚህ አንፃር መሆን ይኖርበታል። አካዳሚክ ሕይወታቸው ምን ይመስላል? እንደ ታሪክ አጥኝ ምን ሠሩ? ምንስ አልሠሩም? "ኀብር ሕይወቴ" በተለይ በሶስት ምዕራፎች (ሰባት፣ ዐሥርና ዐሥራ አንድ) የጸሐፊውን የሶስት ዐሥርት ዓመታት (ከ1963 እስከ 1994 ዓ.ም.) የማስተማር፣ የምርምርና የዩኒቨርሲቲ ተቋማት የመምራትን ሥራ ይዘረዝራል። ከነኝህም ውስጥ ሦስት አንኳር ጉዳዮችን ማንሳት ይቻላል።

**አንደኛ፤ ተምሳሌታዊነትን በተመለከተ**

የምርምር ሥራዎችን በተመለከተ የታሪክ አጥኝው በተለያዩ ጉዳዮች፣ ከባቢዎችና ጊዜዎች የተዋቀሩ ጥናቶችን፣ የተለያዩ መረጃዎችን ከሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ሰብስቦ በታሪክ የአጠናን ዘዴ በማጥናት አዳዲስ የታሪክ ዕውቀቶችን ለአንባብያን አስተዋውቀዋል። በቁጥር ዐሥራ አንድ መጻሕፍትና ወደ ሃምሳ የሚሆኑ የመጻሕፍት ምዕራፎችና መጣጥፎች ሲሆኑ፤ ሥራዎቹ በጥልቅ ጥናት ላይ የተመሠረቱ፤ ሚዛናዊ የሆኑና የጎደሉ ወይንም ትኩረት ያልተሰጣቸውን ታሪኮችና ዕውቀቶች የሚሞሉ ናቸው። የተጻፉባቸው መንገድና ቋንቋም ቀለል ያሉ፣ ግልፅ የሆኑ፣ አጭርና ያልተንዛዙ ናቸው። አንዳንዶቹ ሥራዎች፣ ለምሳሌ *A Quest for Socialist Utopia: The Ethiopian Student Movement, c. 1960-1974* (2014)፣ ከጡረታ በኋላ የተጻፉ መሆናቸው የጡረታ ጊዜ የሥራም ጊዜ እንደሆነም ያሳየ አጋጣሚ ሆኗል። በተለይ ደግሞ አጥኝው የኢትዮጵያ ታሪክ ጥናት ምንጩም ሆነ ዋና ተደራሹም ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን በማመን በእንግሊዝኛ የተጻፉትን መጻሕፍት (*A History of Modern Ethiopia, 1855-1991; Pioneers of Change in Ethiopia: The Reformist Intellectuals of the Early Twentieth Century*) የሀገሪቱ ዋና ቋንቋ ወደ ሆነው አማርኛ ራሳቸው በመተርጎም ከዩኒቨርሲቲ ውጪ ባለው ማኅበረሰብ ዘንድ የታሪክ ዕውቀት እንዲሰፋና በዕውቀት ላይ የተመሠረተ የታሪክ ውይይት እንዲለመድ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

**ሁለተኛ፤ ተከታታይነትን ወይንም ቀጣይነትን በተመለከተ**

ይህንን በሁለት መንገድ ማየት ይቻላል:: አንደኛ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ትምህርት ክፍል የሀገሪቱ የታሪክ ምርምርና ሥልጠና ዋነኛ ማዕከል በመሆኑ ክፍሉን ለማጠናከርና ለማስቀጠል የተሰሩ ሥራዎችን ይመለከታል:: በአንድ በኩል የሁለተኛ ዲግሪ የያዙ የትምህርት ክፍሉ ባልደረቦች የዶክትሬት ዲግሪ ትምህርት እንዲማሩ የውጭ ትምህርት ዕድል ማፈላለግ ሲሆን፤ በሌላ በኩል በዘላቂነት በትምህርት ክፍሉ ውስጥ የሦስተኛ ዲግሪ ሥልጠና መርሀ ግብር ማስጀመር ነበር:: የ"ኅብር ሕይወቴ" ጸሐፊ ሁለቱንም ኃላፊነቶች በመውሰድ በተለይም የዶክትሬት ዲግሪ ስልጠና መርሃ ግብሩን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን ቀርፀውና አስፀድቀው እ.ኤ.አ. በ1990 ዓም ለማስጀመር በቅተዋል:: በዶክተር አድሃና ኃይሌ የጀመረው መርሀ ግብር ባለፉት ሦስት ዐሠርት ዓመታት ትንሽ የማይባሉ ተማሪዎችን ከራሱ ክፍልና ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች በመቀበል እያስተማረ ለታሪክ ጥናት ሙያ ቀጣይነት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረገ ይገኛል:: በሁለተኛነት የሚጠቀሰው በትምህርት ክፍሉና ከዛም ውጭ ባሉ የታሪክ ተመራማሪዎች የሚደረጉ ጥናቶች የሚቀርቡባቸውና የሚታተሙባቸውን መድረኮች በመፍጠር ወይንም በማመቻቸት የሠሯቸው ሥራዎች ነው:: የታሪክ ትምህርት ክፍል ለረጅም ዓመታት በቋሚነት በየሁለት ዓመት የተሳኩ የታሪክ ምርምር ሙያዊ ሴሚናሮችን ከማካሄድ በተጨማሪ የተመረጡ የምርምር ሥራዎችን እያሳተመ ለአንባብያን ያቀርብ ነበር:: የ"ኅብር ሕይወቴ" ደራሲ በነኝህ ወሳኝ ሥራዎች ውስጥ ቁልፍ ኃላፊነቶችን በመያዝ (ለምሳሌም የሴሚናር አዘጋጅና የመፅሔቱ አርታኢ በመሆን) ለሙያውና ለኢትዮጵያ ታሪክ ጥናት ትልቅ አስተዋፆኦ አበርክተዋል:: በተጨማሪም የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ኃላፊ ሆነው ባገለገሉባቸው ዓመታት በየሦስት ዓመት በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ውጭ የሚካሄዱ ዓለም አቀፍ የምርምር ስብሰባዎችን በማዘጋጀት፣ በመምራት፣ የጥናት ሥራዎችን በማቅረብ በተጨማሪም የቀረቡትን ሥራዎች በመሰነድና በማሳተም ሙያውም ሆነ የኢትዮጵያ ታሪክ ጥናት እንዲጎለብትና በፅኑ መሠረት ላይ እንዲቆም የበኩላቸውን ሚና ተጫውተዋል ቢባል ማጋነን አይሆንም::

**ሦስተኛ፤ የአደባባይ ምሁራዊ ተሳትፎን በተመለከተ**

በመጨረሻም ጸሐፊው በሲቪል ማኅበረሰቡ ውስጥ የነበራቸው ተሳትፎ አካዳሚክ ምሁራን (እና አካዳሚያዊ ሥራዎችም) በዩኒቨርሲቲ የታጠሩ ደሴቶች ሳይሆኑ እንደ "አደባባይ ልሂቃንም" ሚና

ያላቸው መሆኑንም  በሚገባ ያሳየ ነው። እንደ የማኅበራዊ ጥናት መድረክ እና የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚን  የመሰሉ በሀገሪቷ ፈር ቀዳጅ የሆኑ ዘርፈ ብዙ የምርምር ተቋማትን በመመሥረትና በመምራት በኢትዮጵያ ውስጥ የዳበሩና ገንቢ የሆኑ ውይይቶች እንዲካሄዱ፣ የተሻሉና ዘላቂነት ያላቸው ፖሊሲዎች እንዲቀረፁና ሀገሪቱም ሆነ ሕዝቧ በጠንካራ ሕዝባዊና ፍትሐዊ መሠረት ላይ እንዲገነባ አግዘዋል። በቅርቡም የኢትዮጵያ የታሪክ ባለሙያዎች ማኅበርን በመመሥረትና በመምራት በሀገሪቷ የሰከነ ሙያዊ የታሪክ ጥናት ውይይቶችና ምርምሮች እንዲካሄዱና እንዲታተሙ፤ ለሕዝቡም እንዲቀርቡ በዛውም የተሻለች፣ ለሁሉም፣ የሁሉም፣ በሁሉም የሆነች ኢትዮጵያን ለመገንባት በሚደረግ ጥረት ውስጥ የራሳቸውን አስተዋፆኦ ለማበርከት ጥረዋል።

## እንደ ማጠቃለያ

የፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ "ኅብር ሕይወቴ" ግለ ታሪክ በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ፣ በኢትዮጵያ ጉዳይ በሚጽፉ፣ በታሪክ ሙያ በሠለጠኑ የታሪክ ተመራማሪዎች ከተጻፉ ግለ ታሪኮች ውስጥ ሁለተኛው ሲሆን፤ በአማርኛ ቋንቋ በመጻፉ ግን የመጀመሪያው ነው ማለት ይቻላል። በዚህ አጅግ መሳጭ በሆነውና ፋይዳ ባለው ግለ ታሪካቸው ልክ እንደ አካዳሚክ ሥራቸው ሁሉ ለኢትዮጵያ የታሪክ ዕውቀት፣ የታሪክ ትምህርትና ምርምር ማደግ፣ መጎልበትና ዘላቂነት ወሳኝ የሆነ አስተዋፅኦ አበርክተዋል። ሌሎች የሙያ ባልደረቦቻቸውም አርዓያነታቸውን በመከተል የኢትዮጵያ የታሪክ ትምህርትና ምርምር ሥራ እንዲያድግና እንዲዘልቅ እንዲተጉ የሚጎተጉት ሥራን አቅርበውልናል።

እንደ መደምደሚያ፣ የደራሲው ግለ ታሪክ ከታሪክ መረጃነት ባለፈ ታሪክ እንደ ታሪክ፣ እንደ የታሪክ አጠናን እና አጻጻፍ ታሪክ ለሚኖረው ውይይትም ሆነ ጥናት ትልቅ ግብዓት ሆኖ ያገለግላልና ሥራው ለሙያው ያለው ጠቀሜታ ቁልፍ መሆኑን ማስገንዘብ ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ የታሪክ ባለሙያዎች በግለ ታሪክና በአካዳሚክ ታሪክ መሃከል ስላለው (ወይንም ስለሌለው) ልዩነትና መመሳሰል፣ በታሪክና በሌሎችም የዕውቀት ዘርፎች ስለሚነሳው የአለ ማዳላት ጉዳይ፣ ግለ ታሪኮች  እንደ አካዳሚክ ሥራዎች ሊወሰዱ ይችላሉ? በአካዳሚክ ግለ ታሪክና በታሪክ መሃከል ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል? አካዳሚክ ግለ ታሪክ እስከምን ድረስ እንደሌላ የታሪክ መረጃነት የታሪክ አጠናን ዘርፍነትና ታሪክና የታሪክ ምንነት የሚታይበት መነፅር ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል? እስከምን ድረስ ነው ግለ ታሪክ ታሪክ ብቻ ሳይሆን የታሪክ አፃፃፍ ጥናት ዘይቤ

የሚሆነው? እና ሌሎችም ጥያቄዎችንና ጉዳዮችን አንስቶ ለመነጋገር የሚረዳ አጋጣሚ የፈጠረ ወይንም ያመቻቸ ሥራ ነውና ጸሐፊውን እያመሰገንን፤ ባልደረቦቻቸውን እያበረታታን ግለ ታሪኮች መጻፋቸው ይቀጥል፤ እነኝህ ሥራዎችንም ሆነ የታሪክ ሙያን በተመለከተ ውይይቶች ይደረጉ፤ ካሉም ይስፋፉ ይበልፅጉ:: ለሙያውና ለዕውቀት ካላቸው ፋይዳ በተጨማሪ ለሀገር ግንባታ የሚኖራቸው ጠቀሜታ ሰፊ ነውና::

ሺመልስ ቦንሳ ጉልማ (ዶ/ር)

ተባባሪ ፕሮፌሰር፤ ስቶኒ ብሩክ ዩኒቨርሲቲ፣ ኒውዮርክ

---

**ኅዳግ ማስታወሻዎች**

[1] እንደ ምሳሌ፣ ካሳዬ ጨመዳ (ብርጋዴር ጄኔራል)፣ *የጦር ሜዳ ውሎዎች ከምስራቅ እስከ ሰሜን* (አዲስ አበባ፣ ብራና ዲዛይንና ህትመት፣ 2007 ዓ.ም.)

[2] ለአብነትም ወልደ ሰማዕት ገብረ ወልድ (ደጃዝማች)፣ *ህይወቴ፡ ለሃገሬ ኢትዮጵያና ለወገኖቼ ኢትዮጵያዉያን ዕድገት የነበረኝ የስራ ጥማት ቅፅ አንድ ( ከ1917 እስከ 1967 ዓ.ም.)* (አዲስ አበባ፣ 2012 ዓ.ም.)

[3] ገብረሥላሴ ኦዳ፤ *ትዝታ ለመታሰቢያ፣ ከሁሉም በጥቂቱ*፤ አዲስ አበባ፣ 1985 እና 1990::

[4] ታደለች ሃይለሚካኤል፣ *ዳኛው ማነው? የብርሃነመስቀል እና የታደለች ሕይወት በኢሕአፓ የትግል ታሪክ* (አዲስ አበባ፣ ኢክሊፕስ ማተሚያ ቤት፣ 2012 ዓ.ም.)

[5] ለአብነት ያህል፣ ሽብሩ ተድላ፣ *ከጉሬዛ ማርያም እስከ አዲስ አበባ፤ የሕይወት ጉዞ እና ትዝታዬ* (አዲስ አበባ፤ ኢክሊፕስ ማተሚያ ቤት፣ 2008 ዓ.ም.)

[6] Taffara Deguefé, *A Tripping Stone: Ethiopian Prison Diary: 1976-1981* (Addis Ababa: Addis Ababa University Press, 2003)

[7] በታሪክ ትምህርት በሰለጠነ ባለሙያ የተጻፈ የመጀመሪያዉ ግለታሪክ በፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስትና በሪታ ፓንክረስት የተጻፈው ነው፡- Richard Pankhurst and Rita Pankhurst, *Ethiopian Reminiscences: Early Days* (Los Angeles: Tsehai Publishers, 2013).

[8] Robert A. Rosenstone, ***The Man Who Swam into History: The (Mostly) True Story of My Jewish Family*** (Austin: University of Texas Press, 2005), xi-xii.